# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 79 ህዳር 10 2002 ዓ.ም


አንብበው
ያስነብቡ!
አባዝተው
ያሰራጩ!

ብ/ጄኔራል አሳምነው ጽጌ ዓይናቸው እስኪጠፋ ድረስ እየተቀጠቀጡ ክብራቸውን የሚነኩ በርካታ ስድቦችን መሰደባቸውና ከሁሉም የባሰባቸው ግን "አማሮች ሽንታሞች ናችሁ" መባላቸው መሆኑን ፍርድ ቤት ውስጥ ተናግረዋል። ምን ዓይነት አንደበት ያለው ሰው ነው እንዲህ ዓይነቱን የዘቀጠ ነገር የሚናገር? ከስደቡ ይልቅ ከእንዲህ ዓይነቱ ዝቃጭ ጋር እኩል ዜጋ መሰኘቱ የሚያሳፍር አይደለምን? . . . ዝርዘሩን ገጽ 2

## በአገራችን ሰቆቃ እንዲያበቃ ወያኔን ማስወገድ ግድ ይላል፤ ለዚህም ተግተን እንሰራለን!

**ከግንቦት 7 የተሰጠ መግለጫ**

መንግሥቴን ለመገልበጥ ሙከራ አድርጋችኋል በሚል በወያኔ ተከሰው እየተሰቃዩ የሚገኙ ወገኖቻችን ላይ እየደረሰው ያለው ሰቆቃ በቃላት መግለጽ እማይቻልበት ደረጃ ላይ ደርሷል። ንቅናቄዓችን ከዚህ በፊትም በዚህ ጉዳይ ላይ ባወጣው መግለጫ በደርግ ጊዜ እንኳን ያልነበሩ የሰቆቃ ዓይነቶች – ለምሳሌ በኤሌክትሪክ ኃይል በሚሞቅ መሳሪያ ጭንቅላት ማጋል – በወያኔ መዳፍ ውስጥ ባሉ የፓለቲካ እስረኞች ላይ ተፈፃሚ እየሆነ እንደሆነ ገልፀን ነበር:: ሰቆቃ መፈጸም በዓለም ዓቀፍ ደረጃ የተገወዘ አረመኔዓዊ ድርጊት ቢሆንም በወያኔ እስር ቤቶች ግን በየጊዜው እየባሰበት የሚሄድ የወያኔ መርማሪዎችና ሰላዮች የእለት ተእለት ተግባር አካል ነው።

ወያኔ ዜጎችን ለማጥቃት ሲፈልግ ወንጀሉንም ማስረጃውንም እራሱ እየፈበረከ ባለበት ሁኔታ በቁጥጥሩ ሥር ያሉትን እስረኞችን ማሰቃየት ለምን ፈለገ? መልሱ አንድ ብቻ ነው – ክፋት!!! በጥላቻ በተለይም በዘረኛ አመለካከት የደነደነ ሥር የሰደደ ክፋት!!!!

ወያኔ ለዘመናት ባካበተው የዘር ጥላቻ እየተነዳ ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ ዘግናኝ ሰቆቃዎችን እየፈጸመ ይገኛል። ወያኔ ሊታረምና ሊሻሻል የማይችል የክፋት ኃይል ነው። መወገድ ይኖርበታል ብለን የምናምነውም ለዚህ ነው።

ትናንት ህዳር 4 ቀን 2002 ዓም በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሁለተኛ ወንጀል ችሎት የተፈፀመው ኩነት በትምህርታዊነቱ የሚጠቀስ ነው። ይህ ችሎት ከህግ ጋር ፈጽሞ ዝምድና የሌለው የወያኔ የክፋት ውሳኔዎችን በህግ ቋንቋ እየቀባባ የሚያቀርብ መድረክ መሆኑ ይታወቃል። ጀግኖቻችን ከወያኔ ፍርድ ቤቶች በተለይም ከዚህ ችሎት ፍትህ እንደማይገኝ አላጡትም። ህዳር 4 ቀን ባደረጉት የተባበረ ጥረት ግን የተደበቀው የእስረኞች ሰቆቃ አደባባይ እንዲወጣ ለማድረግ ችለዋል። (**ወደ ገጽ 2 ዞሯል**)

## የአውሮፓ ህብረት ወያኔ የሚያዘጋጀውን ምርጫ ተብዬ ድራማን ለይስሙላ ለመታዘብ እንደሚመጣ የግንቦት ሰባት የዲፕሎማቲክ ምንጮች ያደረሱን ዘገባ ገለጸ

እንደ ዲፕሎማቲክ ምንጮቻችን ዘገባ የአውሮፓ ህብረት ወያኔ በመጪው ግንቦት ለሚያደርገው የይስሙላ ምርጫ የተለሳለሰ አቋም ለመያዝ መስማማቱን አጋልጠዋል። የአውሮፓ ህብረት የምርጫ ታዛቢዎች ብድን ምርጫ ከመጀመሩ ጥቂት ቀደም ብሎ እንደሚመጣ የተገለጸ ሲሆን የምርጫ ታዛቢው ቀደም ብሎ አለመገኘት በራሱ የአውሮፓ ህብረት ሊወስደው የፈለገው አቋም አመላካች ነው ተብሎአል። ምርጫ የሚጭበረበረው በእለቱ ለት እና በቆጠራ ጊዜ ብቻ ሳይሆን በመራጮች እና በእጩዎች ምዝገባ፣ በቅስቀሳ እና በአጠቃላይ ከምርጫው በፊት ባሉ እንቅስቃሴዎች መሆናቸው ይታወቃል ያሉት የዲፕሎማቲክ ምንጮቻችን የአውሮፓ ህብረት የታዛቢዎች ብድን ግን ምርጫ ጥቂት ጊዜ ብቻ ሲቀረው መጥቶ ስለምርጫው አጠቃላይ ሁኔታ ለመናገር ተዘጋጅቶአል ብለዋል። አንድ የምርጫ ታዛቢ ብድን ከምርጫ ከመደረጉ ከወራት በፊት የተወሰኑ አባላቱን ልኮ የምርጫ ሂደቱን እንደሚከታተል የታወቀ ሲሆን የአውሮፓ ህብረት ግን ተቃራኒውን መውሰዱ የዲፕሎማቲክ ምንጮቻችን አስገርሟል።

መንግሥት አልባ በሆነቺው ጎሬቤት አገር ሱማሌ ውስጥ ላልፉት 20 አመታት የዘለቀው የእርስ በርስ ጦርነት በፈጠረው አለመረጋጋት እና የወያኔ ሱማሌን መወረር ተከትሎ የአክራሪነት አቋም አለው የሚባልለት አልሸባብ እየተጠናከረ መምጣት ምዕራባዊያን ክልሉ የአልካይዳ መተላለፊያ እንዳይሆን ከፍተኛ ስጋት ፈጥሮባቸዋል፡ ለዚህም መፍተሄው በአፍሪካ ቀንድ ከፍተኛ የሡራዊት ብዛት አንዳለው ከሚታወቀው መለስ ዜናዊ ጋር በዲሞክራሲና ሰብዓዊ መብቶች ረገጣ ምክንያት መካረሩን አርግቦ መንግስታዊ ግንኙነት (**ወደ ገጽ 2 ዞሯል**)

ግዜ – ግንቦት 7 ዜና

## የጄ/ል አሳምነው ጽጌ አንድ አይን በእስርቤት በደረሰባቸው ድብደባ ጠፋ ግንቦት 7 ድርጊቱን በማውገዝ ጥሪ አስተላልፏል

ከግንቦት 7 ጋር በማበር መፈንቅለ መንግሰት ለማድረግ ሞክረዋል ተብለው በወያኔ የተለመደ ቅጥፈት ከተያዙት እስረኞች መካከል፣ ጄ/ል አሳምነው ጽጌ ከፍተኛ የሆነ ድብደባ እንደተፈጸመባቸውና በድብደባውም አንድ አይናቸው መጥፋቱን ወያኔ የተቃዋሚዎቹን ሞራል ለማዳሸቅ ለሚጠቀምበት የይስሙላ ፍ/ቤት ተናገሩ። የችሎቱን ውሎ የተከታተለው ሪፖርተራችን የላከልን ዘገባ እንዲህ ይነበባል

"የወያኔ የይስሙላ ችሎት በትናንትናው እለት ውሳኔ ለመስጠት ቀጠሮ ይዞ የነበረ ቢሆንም አሁንም በተለመደው የፋይል መብዛት ሰበብ ለሚመጣው ሀሙስ ቀጠሮ ይዟል። ችሎቶ ቀጠሮ ሰጥቶ ለመበተን ሲዘጋጅ የጄ/ል አሳምነው ጽጌ ጠበቃ ደምበኛየ በእስርቤት ውስጥ ከፍተኛ ድብደባ ተፈጽሞባቸዋል ሲሉ አቤቱታ አቀረቡ። ፍርድቤቱ ግን እንዲህ አይነት አቤቱታ መቅረብ ያለበት ለማረሚያቤቱ አስተዳደር ነው የሚል ምላሽ ሰጠ። እስረኞች ግን በአንድ ላይ ሆነው እንደመጥ የሚል ተቃውሞ አሰሙ። ጄ/ል አሳምነው ፍርድቤቱ አቤቱታቸውን እንዲያዳምጣቸው በልመና መልክ ሲጠይቁ ፍርድቤት ተብዬው በማቅማማት ጥያቄያቸውን ተቀበለ። ጄ/ል አሳምነውም እድሉን እንዳገኙ ብድግ አሉና "በቤተሰቦቼ ላይ የዘር ማጥፋት ወንጀል እየተፈጸመ ነው፣ ቤተሰቦቼ የሚበሉት አጥተው በርሀብ እንዲሞቱ እየተደረገ ነው ብየ ባለፈው ሳምንት ለችሎቱ ከተናገርኩ በሁዋላ ወደ እስር ቤት እንደተመለስኩ ልገልጸው የማልችል ከፍተኛ የሆነ ኢሰብ'ዓዊ ድብደባ ተፈጽሞብኛል። የተወለድኩበት ዘር ጭምር እየተሰደበና እየተንቋሸሸ ነው ድብደባው ይተፈጸመብኝ። በድብደባውም የግራ አይኔ ጠፍቷል; ጉሮሮዬ ተጎድቷል ብለው የደረሰባቸውን ጉዳት እያሳዩ በመረረ ሀዘን ተናገሩ። (**ወደ ገጽ 4 ዞሯል**)

## አንጋፋው ኢሰመጉ በርካታ ሰራተኞቹን ቀነሰ፣ የመዘጋት አደጋ አንዣብቦበታል

በኢትዮጵያ ብቸኛ የሆነው የሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅት የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ በምህጻሩ ኢሰመጉ ወያኔ የሲቪል ማህበራትን ለማሽመድመድ ባወጣው አዲሱ አፋኝ ህግ የተነሳ በርካታ ሰራተኞቹን ለመቀነስ መገደዱን ምንጮቻችን የላኩት መረጃ አመለከተ። ሀምሳ አምስት ሰራተኞች የነበሩት የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ ኢሰመጉ አርባ ሰራተኞቹን አሰናብቶ በአሁን ሰአት በአስራ አምስት ሰራተኞች ብቻ እንደሚንቀሳቀስ ታውቋል።

አለምአቀፍ ከበሬታ እና ተደማጭነት ያለቸውን የሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች እና ሉሎች የሲቪል ማህበራትን ለማሽመድመድ በማሰብ ወያኔ ድርጅቶቹ ከገቢያቸው ከአስር ከመቶ ያልበለጠውን ብቻ ከውጪ እርዳታ ማግኘት እንደሚችሉ መደንገጉ ይታወሳል። ከዘጠና ከመቶ በላይ የሚሆነውን ወጪያቸውን ከውጪ ሀገር በሚገኝ እርዳታ እንደሚሸፍኑ በሚታወቁት የሲቪል ማህበራት ላይ ወያኔ አፋኙን ህግ ለማውጣት የፈለገው በሀገሪቱ እሱ ከሚቆጣጠራቸው ተቋማት ውጪ ያሉ ሌሎች ተቋማት በጭራሽ እንዳይኖሩ ለማድረግ ካለው ስታሊናዊ እምነቱ እና ሲቪል ማህበራት ህዝቡን እንዳያስተምሩ እና የሚፈጽመውን አረመኔያዊ ግፍ እንዳያጋልጡ በመፍራት እንደሆነ በተደጋጋሚ መዘገባችን ይታወሳል።

የመዘጋት አደጋ የሚያንዣብበት የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ ወያኔ በዜጎች ላይ የሚፈጽመውን ፋሺስታዊ ጭፍጨፋ ሳይታክት ሲያጋልጥ መቆየቱ ይታወቃል።ኢሰመጉ በሚያወጣው አመታዊ ሪፓርት ከመኖሪያ መንደራቸው በድንገት ተጠልፈው የደረሱበት ያልታወቁ፣ በብልታቸው ላይ ብሎኬት እና ሌሎችም ነገሮች ተንጠልጥሎባቸው ከፍተኛ ጉዳት የደረሰባቸው፣ጥፍራቸው በፒንሳ የተነቀሉ፣ እስኪተለተሉ የተገረፉ እና የተገደሉ ንጹህን ዜጎችን በፎቶግራፍ ጭምር በታጋዘ መረጃ ሲያጋልጥ መቆየቱን አለም በሙሉ የሚያውቀው ነው።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ወያኔ በነጻው ፕሬስ አባላት ላይ የሚያደርሰው መረን የለቀቀ ግፍ እና ወከባ ተጠናክሮ መቀጠሉ ታወቀ። ያቀደው ነገር እየተከሸፈበት ፣ያመነው እየከዳው እና በአባላቱ ሳይቀር ያለው ተቀባይነት በከፍተኛ ፍጥነት እየተሸረሸረበት ያለው የዘረ ች ስብስብ የሆነው ወያኔ በጋዜጠኞች ላይ ከከፍተኛ ዛቻ አንስቶ ድብደባ እንደሚፈጽም ታውቋል።ሀገሪቱ ውስጥ ያሉት በጣት የሚቆጠሩ ጋዜጦች የመዘጋታቸው ጉዳይ ያለቀለት እንደሆነ የሚናገሩት ምንጮቻቸን በተለይ ሁኔታ የጋዜጦቹን ጉዳይ የሚከታተሉት በረከት ስምኦን እና ሺመልስ ከማል መሆናቸውንም ገልጸዋል።የመዘጋታቸው ጉዳይ አጠያያቂ አይደለም ከሚባሉት ጋዜጦች መካከል አዲስ ነገር እና አውራምባ ታይምስ ዋነኞቹ እንደሆኑ ተጠቁሟል።

## የሕዝብ ቁጣ በዘረኞችና ሰቆቃ ፈፃሚዎች ላይ ይወርዳል፤ ያኔ "ታዝዤ ነው የፈፀምኩት" ማለት አያድንም !!!

አምረን እየታገልነው ያለው ወያኔ ራሳቸውን ጀግኖችና ምርጦች አድርገው በመውሰድ የሚኩራሩ፤ "የጀግንነታቸው" ምንጭ ደግሞ ዘራቸው እንደሆነ ከልብ ያመኑ የስነልቦና ችግር ያለባቸው ሰዎች ስብስብ ነው። እነዚህ ድውያን በውስጣቸው ባለው የትንሽነት ስሜት ምክንያት በአስተሳሰብም ሆነ በሙያ የሚበለጣቸውን ሰው ማዋረድና ማሰቃየት ያስደስታቸዋል። እነዚህ ሰዎች በሃብት እንጂ በመንፈስ አላደጉምና እራስን ከሌላው ጋር እኩል አድርጎ የማየት ብቃት እና ሆደሰፊነትን ማዳበር አልቻሉም።

መንግሥቱን ለመገልበጥ ሙከራ አድርጋችኋል በሚል በወያኔ ተከሰው እየተሰቃዩ የሚገኙ ወገኖቻችን ላይ አስከፊ ሰቆቃ እያደረሰ ያለው ይኸው ከመንፈስ–ትንሽነት የሚመነጭ የስነልቦና ቀውስ ነው።

ብ/ጄኔራል አሳምነው ጽጌ ዓይናቸው እስኪጠፋ ድረስ እየተቀጠቀጡ ክብራቸውን የሚነኩ በርካታ ስድቦችን መስደባቸውና ከሁሉም የባሰባቸው ግን "አማሮች ሸንታሞች ናችሁ" መባላቸው መሆኑን ፍርድ ቤት ውስጥ ተናግረዋል። ምን ዓይነት አንደበት ያለው ሰው ነው እንዲህ ዓይነቱን የዘቀጠ ነገር የሚናገር? ከስደቡ ይልቅ ከእንዲህ ዓይነቱ ዝቃጭ ጋር እኩል ዜጋ መሰኘቱ የሚያሳፍር አይደለምን? ወያኔዎች በሰው ፊት ላይ የሚተፉ ባለጌዎች መሆናቸውን ድሮም እናውቃለን። አንድን ሕዝብ "ሸንታም" ማለት ግን ከብልግናም በላይ ነው።

የወያኔ ቅልብ አግዓዚዎች በበደኖ፣ በአዋሳ፣ በሀረር፣ በጋምቤላ፣ በጎንደር፣ በኦጋዴን፣ በአዲስ አበባ እና በሶማሊያ የጅምላ ጭፍጨፋና የዘር ማጥፋት ወንጀል ሲፈጽሙ በተመሳሳይ የጅምላ ስድብ እየተበረታቱ እንደነበር እናውቃለን። ይህ የትንሽነት ስሜት የፈጠረው የስነ ልቦና ቀውስ በቶሎ መፍትሄ ካልተበጀለት መጨረሻው የከፋ ይሆናል።

ሰቆቃ መፈፀም ዓለም ዓቀፍ ወንጀል ነው። በመሆኑም ዛሬ በወገኖቻችን ላይ ዘግናኝ ሰቆቃዎችን በማድረስ ላይ የምትገኙ የወያኔ ቅጥረኞች በሙሉ ነገ በገባችሁበት ገብተን ዋጋችሁን እንድታገኙ የምናደርግ መሆኑ በጥብቅ ልናስገነዝባችሁ እንወዳለን። ሰቆቃ ፈጽሞ ማምለጥ እንደማይቻል በቁጥጥራችሁ ሥር ካለው ቀልቤሳ ነጌዎ ትምህርት ውሰዱ እንላለን።

አንድን ዘር በጅምላ ማንቋሸሽና በዚህም ምክንያት ግለሰቦችን ማጥቃት ደግሞ ከላይኛው የባሰ ዓለም ዓቀፍ ወንጀል ነው። ለነፃነት እየከፈሉት ባለው የህይወት መስዋዕትነት የምናደንቃቸው ጀግኖቻችን በዘራቸው ምክንያት መሰደብና መደብደብ ያንገበገበን መሆኑን እንድታውቁት እንፈልጋለን።

ሰቆቃንንና የዘር ጥላቻን አድበስብሳችሁ የምታልፉ የወያኔ ካድሬ–ዳኞች፣ አቃብያነ ህግ፣ ፓሊሶችና ሌሎችም ሹማምንት ተገቢውን ቅጣት የምታገኙበት ቀን ቅርብ መሆኑን እናስገነዝባለን።

ግንቦት 7 የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ደጋግሞ እንደገለፀው ይህንን እኩይ ሥርዓትና ባህል ያመጣብንን ወያኔን የማስወገድ ኋላፊነት የወደቀው የበደሉ ገፈት ቀማሽ በሆነው በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ነው። ይህን ግፍና ውርደት ማስቆም የሚችለው የተደራጀ የሕዝብ ትግል ነው። በታሳሪዎች እና በሌላውም ሕዝባችን ላይ እየተፈፀመ ያለው ሰቆቃ እንዲያበቃ ወያኔን ከሥልጣን ማባረርና በምትኩ ለሰብዓዊ መብቶች ክብር ያለው ፍትሃዊ ሥርዓት መመሥረት ይኖርበታል። ግንቦት 7 የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ ቆርጦ ተነስቷል፤ ለዚህም መላው ሕዝብ በጋራ እንዲነሳ ጥሪ ያደርጋል።

ሰቆቃና ዘር ላይ ያነጣጠረ ጥቃትን ማድረስ በሰብዓዊነት ላይ የሚፈፀሙ ዓለም ዓቀፍ ወንጀሎች በመሆናቸው ይዋል ይደር እንጂ የማይቀር እና በይቅርታ የማይታለፉ ተጠያቂነትን በውስጣቸው ይዘዋል። በእነዚህ ወንጀሎች የተሳተፋችሁ ሁሉ መጠየቃችሁ በፍጹም አይቀርም። ያ ቀን ደግሞ ቅርብ ነው። ያኔ "ታዝዤ ነው የፈፀምኩት" ማለት ተቀባይነት አይኖረውም። ሽራፊ እንኳን ህሊና ያላችሁ ካላችሁ እጃችሁን ሰቆቃ ከመፈጸም አውጡ፤ ሰቆቃን አጋልጡ፣ ታገሉ። አለበለዚያ ግን የሕዝብ ቁጣ በእናንተ ላይ ይወርዳል።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

## በአገራችን ሰቆቃ እንዲያበቃ ወያኔን ማስወገድ . . . ከገጽ 1 የዞረ

ሁሉም ታሳሪዎች በጋራ በመቆምም አፋቸውን ሊዘጓቸው ያሰቡትን ዳኞችን በመንፈስ ብርታት አሸንፈው የደረሰባቸው ሰቆቃ ለመላው ዓለም የማስረዳት እድል አግኝተዋል። ብ/ጄኔራል አሳምነው ጽጌ የዳኞቹን ክልከላ ተጋፍተው የደረሰባቸውን አውሬዓዊ ድብደባ በማብራራት የግራ ዓይናቸው መጥፋቱን እና የአንገት ሃብላቸው ከአንገታቸው ቆዳ ጋር አብሮ መወሰዱን አብራሩ። ከዚህም በተጨማሪ ደብዳቢዎቻቸው ዘራቸውን እያንቋንሸሹ እንደቀጠቀጧቸው በመግለጽ የድብደባው ዋነኛ ምክንያት ምን እንደነበር እንድናውቅ አደረጉን። በተመሳሳይ ሁኔታም ሻለቃ መኮንን ወርቁም የደረሰባቸው ድብደባ ዘረዘሩ፤ በአካሎቻቸው ላይ የደረሰውንም ጉዳት አሳዩ። ብ/ ጄኔራል ተፈራ ማሞ፣ ብ/ ጄኔራል አሳምነው ጽጌ እና ሻለቃ መኮንን ወርቁ በሰቆቃ የተጎዱ አካሎቻቸውን እያሳዩ በቁጭት ያደረጓቸው ንግግሮች፤ የሌሎች ጓዶቻቸው ቁርጠኝነት እና በአዳራሹ የታደመው ሕዝብ ስሜት ተደማምረው አሻንጉሊቶቹ ዳኞች መናገር አስቻላቸውና የእስር ቤቱን አለቃ ማብራሪያ እንዲሰጥ ጠየቁት። የእስር ቤቱም አለቃ "እኔም ከእናንተ ጋር አሁን ገና መስማቴ ነው" ሲል ተሳለቀ። አሻንጉሊቶቹ ዳኞች ከዚህ በላይ መጠየቅ አልቻሉም – መመሪያ መቀበል አለባቸውና ነገሩን በቀጠሮ አሳደሩት። በታጋዮቻችን ላይ እየደረሰ ባለው ሰቆቃ እጅግ የተቆጨን ቢሆንም በመንፈስ ጥንካሬዓቸው ኮርተናል።

ከእስር ቤት ውጭም በታሳሪዎች ዘመዶች ላይ ተከታታይ ወከባና እንግልት እየተፈፀመባቸው እንደሆነ የሚደርሱን መረጃዎች ያረጋግጣሉ። ወያኔ በአንድ በኩል ከተቀናቃኞቹ ጋር ስምምነት እየፈጠረ ያለ የሚያስመስል ማጭበርበሪያዎችን እየከወነ በሌላ በኩል ደግሞ ዘርን መሰረት ያደረገውን ጥቃት በከፋ ሁኔታ ቀጥሎበታል።

በታሳሪዎቻቸን ብርታት የወያኔ እስር ቤቶች የሰቆቃ መፈጸሚያዎች የመሆናቸው ሃቅ ይፋ ሆኗል። እስካሁን እያዩ እንዳላዩ ዝምታን ሲመርጡ የነበሩ ዓለም ዓቀፍ የሰብዓዊ መብት ጥበቃ ድርጅቶች፤ ዓለም ዓቀፍ ተቋማትና መንግሥታት ድምፃቸውን እንዲያሰሙ እንጠይቃለን። በውጭ አገራት የሚገኙ ኢትዮጵያዊያንና የኢትዮጵያ ወዳጆች ዘር ላይ ያተኮረ ሰቆቃ በወያኔ እስርቤቶች ውስጥም ውጭም እየተፈጸመ መሆኑ የማሳወቅ ዘመቻዎችን እንዲያፋፍሙ እንጠይቃለን።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ሙሉ ትኩረቱንና ኃይሉን ይህንን የከፋት ምንጭ የሆነውን ወያኔን በማስወገድ በምትኩ ፍትህ የሰፈነባት ነፃይቱን ኢትዮጵያን በመገንባት ትግል ላይ እንዲያውል ጥሪ እናደርጋለን። በአገራችን ሰቆቃ እንዲያበቃ ወያኔን ማስወገድ ግድ ይላል፤ ለዚህም ቀና ሌሊት ተግተን እንሰራለን።

## የአውሮፓ ህብረት ወያኔ የሚያዘጋጀውን ምርጫ ተብዬ . . . ከገጽ 1 የዞረ

መቀጠል አንደ ብቸኛ አማራጭ ተወስዶአል የሚሉት ምንጮቻችን በተለይ እንግሊዝ፣ ጀርመንና ጣሊያን የዚህ አቋም አራማጆች መሆናቸውን አልሸሸጉም።

በአሁኑ ጊዜ በአገር ውስጥ ሰላማዊ ትግል አናካሂዳለን የሚሉ የፖለቲካ ድርጅቶች ከቀን ወደ ቀን እየተፈረካከሱ መሄድ በተለይም በቅርቡ ከወያኔ ጋር የሥነምግባር መመሪያ ተብዬውን በተናጠል የፈረሙ ሶስት ድርጅቶች የሴራው ተባባሪ አልሆን ባሉት የመድረክ አባላት ላይ በከፈቱት ዘመቻ በሰላማዊ ትግል ለውጥ ሊያመጣ ይችላል ተብሎ የሚታመን ጠንካራ ተቃዋሚ የለም ከሚል ድምዳሜ አንዳደረሳቸውና በዚህም የተነሳ የአውሮፓ ህብረት በዘረኛውና አምባገነኑ መለስ ዜናዊ አገዛዝ ላይ እየተለሳለሰ መምጣቱን እነኚሁ ምንጮች ገልጸዋል። ህብረቱ እመራበታለሁ ከሚለው መሰረታዊ አቋም አፈንግጦ ከፋሺስቱ መለስ ዜናዊ አገዛዝ ጋር መሞዳሞዱ በጣም አሳዛኝ እንደሆነ የገለጹት ምንጮቻችን የአውሮፓ ህብረትም ሆነ አሜሪካ ከአገሮች ጋር የሚያደርጉት ግንኙነት አለኝ የሚሉትን ጥቅም በሚያስቀድም መልኩ ስለሆነ ሊደንቀን አይገባም ይልቁንም ለነጻነታችን የሚናደርገውን ትግል በማጠናከር ወያኔ ወደ ከርሰ ምድሩ እየገባ መሆኑን ስናሳያቸው ወዲያው ይታጠፋሉ ብለዋል።

**በግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ የህዝብ ግንኙነትና ቅስቀሳ ዘርፍ በሳምንት አንዴ የሚዘጋጅ ድርጅታዊ ልሳን**

**የፖስታሳጥን ቁጥር :-** POBox: 4916
2003EX Haarlem, The Netherlands

# ‘አፍሪቃ ለዓለም ህብረተሰብ ያልተበከለ የሃይል ምንጭ ትሆናለች’ የሚለው የመለስ ዜናዊ አዲሱ ዜማ ለምን ይሆን?

አዲስ አበባ ላይ በቅርብ ቀን በተካሄደው ዓመታዊ የአፍሪቃ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን ኮንፈረንስ ላይ የወያኔ ኢሃዴጉ ቁንጮ መለስ ዜናዊ ባደረገዉ የተለመደና ብልጣብልጥነት የተሞላበት ንግግሩ በአየር ንብረት ለዉጥ ምክንያት ባዓለማችን ላይ ያንዣበበዉን ችግር ከመቅረፍ አንጻር የዓለም ዓቀፉ ህብረተሰብ ለችግሩ ብዙም ቁብ አልሰጠውም በማለት ዘመን አመጣሽ ዉንጀላዉን ካቀረበ በኋላ የዓለማችን ሃብታም አገራት ደኅስ ያለ የገንዘብ ድጋፍ በማድረግ ታዳጊ ሃገሮችን ካለባቸው የድህነት ጫና ሊያላቅቋቸው ይገባል በማለት ትእዛዝ አዘል መልእክቱን አስተላልፏል። ይህን እያወራ ባለበት ሁኔታ አንዳንድ የአካባቢ ሳይንስ አዋቂዎች ያቀረቡት በሃብት የበለጸጉት አገሮች የዓለማችንን ከባቢ አየር ላቆሸሹበት ማካካሻና ለተፈጠረዉም የአየር ንብረት መዛባት የማስተካከያ ርምጃ መውሰጃ ይረዳ ዘንድ ለአፍሪቃ በየዓመቱ ወደ አንድ መቶ ቢሊዮን ዶላር መክፈል ይገባቸዋል የሚለው ሃሳብ በአይነ ህሊናዉ እየታየውና ከዚህም በርካታ ገንዘብ ውስጥ ወደሱ ህገወጥ መንግስት ካዝናና ባለስልጣኖቹ ኪስ ሊገባ የሚችል አዲስ የገቢ ምንጭ መሆኑን እያሰላ ነበር። መለስ በዚህ ኮንፈረንስ ላይ አይናገረው እንጂ በኢትዮጵያ ላይ በተደጋጋሚ እየደረሰ ላለዉም በሚሊዮኖች የሚቆጠር ህዝብ በረሃብ አለንጋ መገረፍ መንስኤው እነኝህ ያደጉ አገሮች የከባቢ አየርን በማቆሸሻቸዉ ምክንያት የተፈጠረው የአየር ንብረት መዛባት ያስከተለዉ ተጽዕኖ ነዉ በሚል መከራከሩ ይታወቃል። ለጋሽ የሚባሉ ሃገራትን ስሜትና ፍላጎት ማጥናትና የነኝሁን አገሮች ቀልብ የሚስብ ወሬ በተለያዩ መድረኮች ማዉራት ዋና ተግባሩ የሆነዉ አምባገነኑ መለስ በዚሁ ስብሰባ ላይ ራሱን የተዋጣለት የአካባቢ ሳይንስ አዋቂ በማድረግና የተመረጡ ሙያዊ ቃላትን በመጠቀም ያደረገው ንግግር በርካቶችን አስገርሟል።

በሚቀጥለዉ ዲሰምበር ወር ኮፐንሃገን ላይ በሚካሄደው የተባበሩት መንግስታት ዓለም አቀፍ ስበሰባ በኪዮቶ ፕሮቶኮል ስምምነት ተደርሶባቸው ተግባራዊ ያልሆኑ ያፈጻጸም ችግሮች ላይ በመወያየት ስምምነት ላይ ይደርሳል ተብሎ የሚጠበቅ ሲሆን ውይይቱም ያተኩርባቸዋል ተብለዉ ተስፋ ከተደረጉባቸው ነጥቦች አንደኛዉ በልማት የበለጸጉ ሃገራት ኢንደስትሪዎች ወደከባቢ አየር የሚለቁትን ካርበንዳዮክሳይድ መጠን እንዲቀንሱ እንዲሁም ይህን ወደከባቢ አየር የሚለቀቅ ጋስ ለሚሸከሙት (ለሚቀበሉ) ታዳጊ ሃገራት ይህን ጋስ ለመሸከም የሚያስችላቸዉን አቅም ይፈጥሩ ዘንድ አስፈላጊዉን የገንዘብ ማካካሻ ድጎማ ማድረግ እንደሆነ ተገልጿል። በዚህም ምክንያት ብልጣብልጡ መለስ በኢትዮጵያ ላይ የዘረጋዉን የግፍ አገዛዝ ሊያራዝምልኝ ይችላል ብሎ የሚያምንበትን የገንዘብ አቅም ለማጎልበት ይችል ዘንድ በዚህ ስብሰባ በመገኘት ሊናገራቸዉ የሚገቡ ‘ወርቃማ’ ኢኮሎጂካል/ ኢንቫይሮመንታል ቃላትን በማጥናት ስራ ላይ ተጠምዶ ይገኛል።

በእድገት ከበለጸጉት ሃገራት ወደ ከባቢ አየር የሚለቀቀውን ካርበንዳዮክሳይድ መሸከም ከሚያስችሉት መንገዶችና ተግባራት ዉስጥ አንዱ የደን ልማትን ማስፋፋት ሲሆን ከዚህ አንጻር የወያኔው ኢሃዴግ መንግስት የኢትዮጵያዊያንን ሚለኒየም ምክኒያት በማድረግ ኢትዮጵያን በአንድ ዓመት ዘመቻ አገሪቱን ያጥለቀለቀበትን የዛፍ ተከላ ሪፖርት የፕሮፓጋንዳ ድራማ ለአብነት እንጥቀስ።

በኢትዮጵያ የሚለኒየሙን የዛፍ ተከላ ዘመቻ አስመልክቶ ወያኔ ኢህአዴግ ተክያለሁ ብሎ ባደባባይ በተባበሩት መንግስታት የኢንቫይሮመንት ፕሮግራም ድረገጽ ላይ ሪፖርት ያደረገው የዛፍ ችግኝ ብዛት ከ700 ሚሊዮን በላይ ሲሆን ባንጻሩ አገር ዉስጥ ባሉ ሚዲያዎችና የመረጃ ምንጮች በወቅቱ ሪፖርት የተደረገው ደግሞ ከአንድ ቢሊዮን በላይ መሆኑ ይታወሳል። በቀረበውም ሪፖርት መሰረት በዓመቱ በዛፍ ችግኝ ተከላ ዘመቻ ዉጤት አሳይተዋል ተብለው ከተዘረዘሩት 12 አገራት ውስጥ ኢትዮጵያ 217 ሚሊዮን ችግኝ በመትከል በሁለተኝነት ደረጃነት የተቀመጠችውን ሜክሲኮን አስከትላ በአንደኝነት መፈረጇ ተገልጿል። ይህ በኢትዮጵያ ተተከለ የተባለው የዛፍ ችግኝ መጠን ሊያርፍበት የሚችለው የቦታ ስፋት ቀላል በሆነ ስሌት (ለአንድ ዛፍ በጣም ዝቅተኛዉን የተከላ ቦታ ስፋት 10 ካሬ ሜትር በማድረግ) ሲሰላ ከ 10 ቢሊዮን ካሬሜትር ወይንም 1 ሚሊዮን ሄክታር ስፋት በላይ ይሆናል ማለት ነው። ይሁን እንጂ ይህን ያህል የዛፍ ችግኝ በርግጥ ኢትዮጵያ ዉስጥ በተገለጸዉ ወቅት ተተክሏል ወይ የሚለዉ ጥያቄ ምላሽ ከማጣቱ ጀምሮ ከዚህ የችግኝ ተከላ ሪፖርትም በሁዋላ ምን ያህሉ በትክክል እንደጸደቀ የተነገረ ነገር ባለመኖሩ (ይገለጻል ተብሎም የሚጠበቅ አይደለም) አፈጻጸሙ ምን ይመስል ይሆን የሚለዉን ጥያቄ ዉስጡን ለቄስ በሚል ልናልፈው እንችላለን። በወቅቱ ኢትዮጵያ ዉስጥ ተተከለ የተባለው የዛፍ ችግኝ ቁጥሩ የተጋነነ ስለመሆኑም ሆነ በትክክል የተገለጸው ስራ ተሰርቷል/ስኬታማ ሆኗል ወይ ብሎ የሚጠይቀው ክፍል እንደሌለ ወያኔ ኢህአዴግ ጠንቅቆ የሚያውቅ የዘፈቀደ መንግስት በመሆኑ የዚህ ሪፖርት ጋጋታ ዓላማ ምን እንደነበረ መገመት አስቸጋሪ አይመስለንም።

ዓለም በግልጽ እንደሚያውቀው ባሁኑ ሰአት በኢትዮጵያ ዉስጥ አለ ተብሎ የሚገመተው የደን ሽፋን ከ3% በታች ሲሆን ይህ የደን ሽፋን መጠን ቀደም ብሎ ከ50 ዓመታት በፊት ከነበረበት 40% የቁልቁሊት ወርዶ አሁን ካለበት ደረጃ መድረሱና በአሳሳቢ ሁኔታ መመናመኑ ሳያንሰን ባሁኑ ሰዓት ወያኔ ኢሃዴግ ለሃብታም ሃገራት ኢንቨስተሮች ለመሸጥ ዝግጁ አድርጊያለሁ ያለው ከ3 ሚልዮን ሄክታር የሚበልጥ ስፋት ያለው ቦታና ለሱዳን መንግስትም አሳልፎ ለማስረከብ ዝግጅቱን ያጠናቀቀለት ተቀራራቢ ስፋት ያለው ለም መሬት በርካታው ክፍል በደን የተሸፈነ እንደሆነ ሙያዊ ዕውቀቱ ያላቸው በርካታ አዋቂዎች ይስማሙበታል። የቤቷ አሮባት የሰው ታማስላለች እንደተባለው ሁሉ መለስ ዜናዊ የግፍ አገዛዙን እያስፋፋባት ያለችዉን ኢትዮጵያ በዚህ መልኩ የተፈጥሮ ሃብቷን እያራቆተ ባለበት ሁኔታ የአፍሪቃ የተፈጥሮ ሃብት ተቆርቁዋሪና ተከራካሪ በመሆን ወደኮፐን ሃገን ማቅናቱ የተሳሳተ ሰው በትክክለኛዉ ቦታ የሚለዉን የእንግሊዝኛ አነጋገር ያስታውሰናል።

በተመሳሳይ መልኩ የወያኔ ኢህአዴጉ ቁንጮ መለስ ዜናዊ በኢትዮጵያ በተደጋጋሚ በህዝብ ላይ እየደረሰ ያለዉን የረሃብ አለንጋ መጠነ ሰፊ ችግር መንስኤ በዋነኛነት የዓለም የአየር ንብረት መዛባት ያስከተለው የዝናብ እጥረት እንደሆነ ለዓለም ህብረተሰብ ለማሳመን ጥረት ማድረጉ ሌላው አስቂኝ ድራማው ነው። ለዚህ አባባላችን እንደምሳሌ መጥቀስ የምንችለው እንደእስራኤል ያሉ ዓመታዊ የዝናብ መጠናቸው ዝቅተኛ የሆኑ ሃገራትን ነው። እነኝህ ሃገራት ህዝባቸው በዝናብ እጥረት ምክንያት በረሃብ አለንጋ ተገርፎ ያለቀበት ጊዜ ተሰምቶም ካለማወቁ አንጻር ሲታይ እንደኢትዮጵያ ያለችን በዉሃ የተፈጥሮ ሃብቷ ከፍተኛነት የምትታወቅ አገር ይዞ በአየር ንብረት መዛባት ምክንያት የተፈጠረዉ የዝናብ እጥረት ብቻ ለነኝህ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ህዝቦች በረሃብ አለንጋ መገረፍ ዋነኛ ምክንያት ነዉ እያሉ ሽፋን ለመስጠት መሞከር አሳፋሪ ነው።

ወያኔ ኢህአዴግ እንደ አንድ ገንዘብ አሳዳጅና አግበስባሽ ነጋዴ ገንዘብ የሚገኝበትን ቦታ የሚያሻትትና የዓለም ሃብታም ሃገራትን የገንዘብ ልገሳ አቅጣጫ ሌት ከቀን በማነፍነፍ መከታተል ዋና ተግባሩ መሆኑ የታወቀ ከመሆኑም በላይ ባሁኑ ሰዓት አገዛዙ ያለበትን የፖለቲካ ኢኮኖሚያዊና ማህበረሰባዊ ቀውስ በተለያዩ ተራና ተቀባይነት የሌላቸው ምክንያቶች በመሸፋፈን ለጋሽ የተባሉ ሃገራትን ቀልብ ለመሳብ እያቀነባበረ ያለውን የማስመሰል ተግባር በተጠናከረ መልኩ በመቀጠል እነሆ አሁን ደግሞ የዓለማችን የአየር ንብረት መዛባት ዋና ተቆርቋሪ መስሎ በመቅረብ ማደናገሩን ተያይዞታል።

ቴረሪዝምን በህዝቦቹ ላይ እያስፋፋ ባለበት ሁኔታ የአፍሪቃን ቀንድ ቴረሪዝም ችግር መፍታት የሚችል ከኔ በላይ የለም በማለቱ ከቡሽ አስተዳደር እጅግ ከፍተኛ የሆነ የገንዘብና ወታደራዊ ርዳታን፤ እንዲሁም በሃገራችን ያሉ መሰረታዊ የድህነት ችግሮች መንሴዎች ባልፈታበት ሁኔታ ኤች አይ ቪ ኤይድስን ጠራርጌ ለማስወገድ ቆርጬና ታጥቄ የተነሳሁ ጀግና ነኝ በማለቱ ከዚችው ከአሜሪካ ዳጎስ ያለ የገንዘብ ርዳታን ወደካዝናው ያስገባዉ የወያኔ ኢሃዴግ መንግስት አሁን ደግሞ ምራቁን እያስዋጠዉ ያለዉን ባለማችን ላይ ያንዣበበዉን የተፈጥሮ አየር ንብረት መዛባት ችግር ማስተካከያ የገንዘብ ድጎማ በእጁ ለማስገባት በመቋመጥ አሰፍስፎ ይገኛል። ወያኔ ኢሃዴግ በዚህ ብቻም አላቆመም፣ ምናልባት የአሜሪካዉ አስተዳደር ፊቱን ካዞረብኝ በሚል ቻይና ለአፍሪቃ ሃገራት ድጋፍ ይሆን ዘንድ በሚቀጥሉት ሶስት ዓመታት ወደ 10 ቢልዮን ዶላር ፈሰስ አደርጋለሁ በማለቷ ይህንንም ገንዘብ ወደ ካዝናዉ ለማስገባትና የድርሻውን ማፈስ ይችል ዘንድ በአፍሪቃ ለደረሰው የኢኮኖሚክ ክራይሲስ መነሻው የአሜሪካ ፋይናንሺያል ሲስተም ውድቀት መሆኑን በመግለጽ አሜሪካን ተጠያቂ ካደረገ በኋላ ለተፈጠረዉ ችግር ብቸኛዋ መፍትሄ ቻይና እንደሆነች በመግለጽና ከቻይና ወዲያ አገር ላሳር ነው በማለት ማሞጋገሱን ተያይዞታል።

ባለፉት የወያኔ ኢህአዴግ 20 የግፍ አገዛዝ ዓመታት ጉዞ ከ10 ሚሊዮን በላይ የሚሆነው የኢትዮጵያ ህዝብ በተደጋጋሚ በረሃብ አለንጋ እየተቀጣ ባለባትና የሃገሪቷም አንጡራ የተፈጥሮ ሃብት ተመዝብሮና ተጎሳቅሎ በሚገኝበት ሁኔታ፤ ገንዘብ አሳዳጁ ግፈኛዉና አምባገነኑ የወያኔዉ ኢህአዴግ ቁንጮ መለስ ዜናዊ በሚቀጥለዉ ወር በኮፐንሃገን በሚካሄደው ዓለም አቀፍ የአየር ንብረት ለውጥ ስብሰባ አፍሪቃን ወክሎ መገኘቱ እጅግ አሳዛኝና አጠያየቂ ነው ብለን እናምናለን። በመሆኑም በእንደመለስ አይነት አምባገነንና በሙስና የተዘፈቀ መሪ ለዓለማችን የአየር ንብረት መዛባት ጠበቃ ቆሚያለሁ፡ አፍሪቃንም የዓለም ህብረተሰብ ያልተበከለ የሃይል ምንጭ አደርጋለሁ የሚል ብልጣብልጥነት የተሞላበት ወሬ ሲያወራ መስማት አሁንም በስልጣኔ አድገናል የሚሉ ለጋሽ ሃገራት መንግስታትን ከማሞኘትና ከዚህም ማጭበርበር የሚገኘዉን ገንዘብ ህዝብን አፍኖና ረግጦ ለመግዛት ወይም የግል ኪስን ለማዳበሪያ ከማዋል የዘለለ ፋይዳ አይኖረውም እንላለን።

## የጄ/ል አሳምነው ጽጌ አንድ አይን .. . . ከገጽ 1 የዞረ

የጄ/ል አሳምነው ጽጌ ንግግር እየተሰማ ባለበት ጊዜ ግን አንድ ያለተጠበቀ ነገር ተፈጠረ። በጀኔራሉ ንግግር የተነኩ ከ300 በላይ ታዳሚዎች ስሜታቸውን መቆጣጠር ተስኖአቸው በአንድ ጊዜ ችሎቱን በለቅሶና በጩሄት አደባለቁት። ወዲያውም በዙሪያው የተኮለኮሉ የፌደራል ፖሊሶች ፍርድቤቱን በመውረር ሰዎችን እየመረጡ ወደ አልታወቀ ቦታ ወሰዱዋቸው። ግርግሩ ቀጥሎ ዳኞቹ ችሎቱን ለማስጀመር ተቸገሩ። የወያኔ ቅልብ ፖሊሶች ተቃውሞውን ከተቆጣጠሩት በሁዋላ ዳኞች ተመካክረው "ባዳራሹ የተገኙትንና ያልተነኩትን ታዳሚዎዎች በአስቸኳይ አዳራሹን ለቀው እንዲወጡ ትእዛዝ አስተላለፉላቸው። ሁሉም ታዳሚዎች ለቀው ከወጡ በሁዋላ ችሎቱ እንደገና ተሰየመ። ከችሎቱ እንደወጣን ባዳራሹ የነበሩት ከ300 በላይ ና ካዳራሹ ውጭ የነበሩት ከ200 በላይ ሰዎች የወያኔን የግፍ አገዛዝ ሲቃወሙ ይሰማ ነበር። አንዳንደቹ 'ከዚህ ፍትህ አልባ ስርአት መቼ ይሆን የምንላቀቀው፣ ከዚህ ጨቋኝ አገዛዝ መቼ ይሆን የምንገላገለው እያሉ ሲናገሩ ይሰማ ነበር። በተለይ አንዲት አዛውንት ድምጻቸውን ከፍ አድረገው ' እግዜሩም ዝም አለን፣ ወዴት አቤት እንበል። ምን ጉድ ነው የላከብን' እያሉ በተደጋጋሚ ሲያማርሩ ተስተውለዋል።"

እስረኞቹ በተደጋጋሚ በዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ላይ የሰላ ትችት ማቅረባቸው የተዘገበ ሲሆን፣ የወያኔ የደህንነት ሰዎችም 'ለምን ትችት አቀረባችሁ፤ የምትፈልጉት የሚዲያ ሽፋን ነው አይደለም' እያሉ እንደእባብ እንደሚቀጠቅጣቸው ታውቋል። ከዚህ በፊት በአንደኛው እስረኛ ላይ የኤሌክትሪክ ማሞቂያ አድርገው ማቃጠላቸውን መዘገባችን የሚታወስ ሲሆን፣ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በፍርድቤቱ ትእዛዝ ድብደባውና ስቃዩ ይቆማል ተብሎ ቢታመንም ድብደባውን ግን ከጊዜ ጊዜ እየከፋ መሄዱን ነው ለማረጋገጥ የተቻለው።

ለወያኔ እንደጠላት ለኢትዮጵያ ህዝብ ግን እንደነጻነት አርበኞች በሚታዩት ላይ የሚደርሰው እንግልትና ስቃይ ሌሎች በወያኔ ላይ ተቃውሞ እንዳያነሱ ለማስፈራራት መሆኑ ቢታወቅም፣ በወያኔ ላይ የሚደርሰው ተቃውሞ ግን አሁንም ተጠናክሮ ቀጥሎአል። በመከላከያ ውስጥ ከፍተኛ ሽኩቻ እንዳለ የሚደርሰን መረጃ የሚያመለከት ሲሆን፣ ወያኔ የተወሰኑ የመከላከያ አባላትን የግንቦት 7 ደጋፊዎች ናችሁ በሚል ማሰር መጀመሩን ከመከላከያ የሚደርሰን ተደጋጋሚ መረጃ ያሳያል።

"አበረታቹ ነገር አብዛኛው የመከላከያ አባላት ስለ ግንቦት 7 ማወቃቸውና ንቅናቄውንም ለመቀላቀል ሁኔታዎችን እየጠበቁ ነው" የሚለው የመከላከያ መረጃ፣ ግንቦት 7 በተግባር ላይ የተመሰረተውን እንቅስቃሴ በሚጀምርበት ጊዜ ያለብዙ ቅሰቀሳ በርካታ የአማራ፣ የኦሮሞ፣ የደቡብ፣ የቤንሻንጉል፣ የጋምቤላ፣ እና የሌሎችንም ክልሎች ወታደሮች ከጎኑ ለማሰለፍ እንደሚችል በመከላከያ ውስጥ ያለውን እውነታ ተንተርሶ የተሰጠው የመከላከያ ትንተና ያሳያል። በመለስ ዜናዊ አንጃ የበላይነት ደስተኛ ያልሆኑ የትግራይ ተወላጅ የመከላኪያ አባላት ቁጥርም ከጊዘ ወደጊዜ እየጨመረ በመምጣቱ የነጻነት ሃይሎች እራሳቸውን የመከላከል እርምጃ መውሰድ በሚጀምሩበት ወቅት የወያኔን ዕድሜ ለማራዘም ህይወቱን አሳልፎ የሚሰጥ ሰው ቁጥር አሁን ከሚገመተው በ'እጅጉ አንደሚያንስ ይጠበቃል።

በተያያዘ ዜናም ወያኔ ወራዳ ተግባሩን ከፈጸመ በሁዋላ ግንቦት 7 ድርጊቱን በጽኑ አውግዟል። ንቅናቄው፣ የኢትዮጵያ ህዝብ ሙሉ ትኩረቱን እና ሀይሉን ይህንን የከፋት ምንጭ የሆነውን ወያኔን በማስወገድ በምትኩም ፍትህ የሰፈነባት ነጻይቱን ኢትዮጵያን በመገንባት ለሚደረገው ትግል እንዲያውል ጠይቋል። ግንቦት 7 ወያኔን ለማስወገድ ቀንና ሌሊት በመስራት ላይ ሲሆን፣ አሁን በተያዘው የትግል እንቅስቃሴና አቅጣጫ ህዝቡ ከተረባረበ ወያኔን ለማስወገድ የሚፈጀው ጊዜ ሩቅ እንደማይሆን ግንቦት 7 በተደጋጋሚ ሲገልጽ መቆየቱ ይታወቃል።

በተያያዘ ዜና ፍዳ እና ሰቆቃ አምራች የሆነው የፋሺስቱ የወያኔ ቡድን "መንግስቴን ሊገለብጡ" ሲሉ ያስዝኳቸው ብሎ በወህኒ ከሚያማቅቃቸው ውድ የኢትዮድያ ልጆች አንዱ የሆኑትን የብርጋዲየር ጄኔራል አሳምነው ጽጌን ግራ አይን በድብደባ ማጥፋቱ ከተሰማ ወዲህ በመላው ዓለም በሚኖሩ ኢትዮድያዊያን ዘንድ ከፍተኛ ቁጣ መቀስቀሱን ለዝግጅት ክፍላችን የሚደርሱን መልእከቶች ያስረዳሉ። በርካቶች በከፍተኛ እልህና በወገናዊ ቁጭት እንደገለጹት መረን የለቀቀው የወያኔ አገዛዝ በቃህ!ሊባል እንደሚገባው የገለጹ ከመሆናቸው በላይ አብዛኛዎቹም ወያኔን በሀይል ለመጣል የሚደረገውን ትግል ከልብ የሚደግፉ መሆናቸውን ገልጸዋል።

ጌቱ ተገኝ የተባሉ በአውሮፓ የሚኖሩ ኢትዮድያዊ "ከዚህ በላይ ልሸከመው የምችል ውርደት የለም። በማንኛውም መንገድ ልታገል ቃል እገባለሁ። እባካችሁ ጀግኖች ወገኖቻችንን ከእናንተው ጋር ነን በሉልን። የቤተሰባቸውንም አድራሻ ብታሳውቁን ተገቢውን እርዳታ ሁሉ ለማድረግ ዝግጁ ነን ብለዋል።"

ሌላው በጀግኖች ወገኖቻችን ላይ የደረሰው ግፍ አስቆጥቷቸው መልእከታቸውን ለዝግጅት ክፍላችን የላኩት ወንድምአገኘሁ የተባሉ ሲሆኑ <<ምንም እንኳን በእነጄኔራል አሳምነው ላይ የደረሰው ብቀላ በጣም ቢያበሳጨኝም በአንድ በኩል ግን ወያኔ የደረሰበትን የመንፈስ ጭንቀት እና መረበሽ ስላሳያኝ ተጽናንቻለሁ። ወያኔ ፍጹም ተስፋ መቁረጥ ውስጥ ባይገባ ኖሮ በእስር ላይ በሚገኙ መኮንኖች ላይ የፋሺስት በትሩን አያሳርፍም ነበር።ዛሬ ነገ ሳልል ወያኔን ለማውረድ በሚደረገው ትግል የአቅሜን ለማበርከት ቃል እገባለሁ>> ብለዋል። አቶ ሙስጠፋ ከድር የተባሉ ደግሞ ሲናገሩ "እነዚህን ሰዎች ቁጭ ብለን ሰቅለናቸው ቆመን ማውረድ እንዴት ያቅተን ካሉ ቦኋላ ብቸኛው አማራጭ ወያኔ ሲመኘው በኖረው እና . . . **ወደ ላይ ይቀጥላል**

ሊገባው በሚችለው የመሳሪያ ትግል ብቻ መግጠም ነው፤ በዚህ ረገድ ሊያደራጀን ለሚሻ ሁሉ ዝግጁ ነን ብለዋል;፤ አክለውም ያገሬ ሰው ዝም ብለህ እስከትሞት አትጠብቅ ተነስና ተፋለማቸው። የተከበረው ዘርህ እየተንቋሸሸ ማንነትህ እየተዋረደ ነው። ከዚህ በላይ ምንም ሞት የለም። ፈሪም ለሆዱ፣ ጎበዝ ለማንነቱ ይኖራል። ጎበዝ ነኝ የምትል ሁሉ ጉብዝናህን የምታሳይበት ጊዜ መጥቷል።" ብለዋል።

ለዝግጅት ከፍላችን የደረሱት በርካታ አስተያየቶች ግፍ አሜን ብሎ መቀበል በማይችል ኢትዮድያዊ እምቢ ባይነት እና በቁጣ የተሞሉ ከመሆናቸውም ባሻገር ህግ አልበኝነትን በህግ የበላይነት፣ ዘረኝነትን በእኩልነት፣ መከፋፈልን በአንድነት ለመተካት የሚደረገውን መራራ ትግል ለመቀላቀል ቃል የገቡ መሆናቸውም ለማየት ተችሎአል።

ለዝግጅት ክፍላችን ከደረሱ በርካታ የቁጣ እና የእልህ መልክቶች በተጨማሪ ኢትዮድያን በተለያዩ ድረ ገጾች ላይ በጀግኖች ወገኖቻችን ላይ እየደረሰ ያለውን ፍጸም አረመኔያዊ እና ፋሺስታዊ እርምጃ በማውገዝ ላይ ናቸው።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የወያኔው የእስረቤት ሹም ፍርድ ቤት ቀርቦ ስለ ጄል አሳምነው ጽጌ ድብደባ መልስ ሰጥቷል። በርካታ ኢትዮጵያውያንም በወያኔው የውሸት መልስ በመበሳጨት ቁጣቸውን እየገለጹ ነው።

ስማቸው እንዳይገለጽ የፈለጉ አንድ የህግ ባለሙያ እንደተናገሩት፣ ወያኔ ግለሰቦቹ ራሳቸውን ጎዱ እንጅ አልተደበደቡም ሲል የሰጠው መለስ ወያኔ እውነት የሚባል ነገር የማይወጣው ሀሰት መናገርን እንደ ፖለቲካ ስልት አድርጎ የሚቆጥር ፓርቲ መሆኑን በተደጋጋሚ ያሳየበት ነው ብለዋል። ወያኔ ምንም እውነት የሆነ ነገር ቢናገር ህዝቡ እንደማያምነው የሚያደርጉት እንደነዚህ አይነት አይን ያወጡ ውሸቶች ናቸው የሚሉት የህግ ባለሙያው፣ ጄ/ል አሳምነው ጽጌ ራሳቸውን ከግድግዳ ጋር አጋጭተው ጎዱ በሚል የተሰጠው መልስ እንኳንስ የተከበሩት ጄኔራል ቀርቶ በሀሺሽ የናወዙት እነመለስ ዜናዊም እስርቤት ቢገቡም እንዲህ አያደርጉም ሲሉ አጣጥለዋል። የወያኔው የማረሚያ ቤት ሀላፊ አበበ ዘሚካኤል ባለፈው ሰኞ ለይስሙላው ፍርድቤቱ ቀርቦ ሲናገር "ግለሰቡ የንብረት እገዳ ትእዛዝ ሲሰጣቸው ራሳቸውን ከግድግዳ ጋር ያጋጩ ነበር" የሚል መልስ መስጠታቸው የሚታወስ ሲሆን፣ በዚህ የደደቦች መልስ አንጀቱ ያላረረ ኢትዮጵያዊ እንደሌለም ታውቋል። ወያኔ እስከመቼ በኢትዮጵያ ህዝብና በፍርድቤት ላይ እንደሚቀልድ አይገባኝም ያሉት የህግ ባለሙያው፣ እነዚህ በስልጣን ላይ ሆነው ያፓርታይድን ስርአት የሚያራምዱት ሰዎች ከትግራይ ህዝብ አብራክ ለመወለዳቸው እጠራጠራለሁ ብለዋል።

የትግራይ ህዝብ ሀይማኖተኛ፣ ውሸትን አጥብቆ የሚጠላ ሆኖ እያለ እነዚህ በስልጣን ላይ ያሉት ጥቂት ዘረኞች ግን ውሸትን ሳይሆን እውነትን የሚጠሉ፣ ህሊናቸውን ሽጠው የበሉ፣ ከሰው በታች የወረዱ ና የረከሱ በመሆናቸው ከዚያ ሀቀኛ ህዝብ አብራክ መውጣታቸውን እጠራጠራለሁ ብለዋል። እኝህ አስተያየት ሰጪ አክለው ሲናገሩ ዳኞች የይስሙላ ዳኞች ባይሆኑ ኖሮ እንዲህ አይነቱን ተራ ዋሾ እንዲጠየቅ ያደርጉ ነበር ካሉ በሁዋላ፣ አሁን ግን ነገሩ ተገልብጦ እውነት ተናጋሪው እውነት በመናገራቸው እንደገና ሊከሰሱ፣ ሀሰት ተናጋሪው ግን ሊሾሙና ሊሸሉሙ ነው ሲሉ የእስረቤቱ ሃላፊ "የማረሚያ ቤቱን ስም በማጉደፋቸው እንጠይቃቸዋለን ሲሉ ለሰጡት መልስ" ምላሻቸውን ሰጥተዋል። በአንድ አገር መንግስት ከሳሽ፣ መንግሰት ደኛና መንግሰት መስክር ሆኖ የሚቀርበው በኢትዮጵያ ብቻ ነው የሚሉት እኚህ አስተያየት ሰጪ፣ መንግስት በማይታመንበት አገር እንዴት ህዝቡ ተማምኖ ፍርድቤት ይሄዳል እንዴትስ ፍትህ አገኛለሁ ብሎ እንዲያስብ ይጠበቃል ሲሉ ጠይቀዋል።

በአሁኑ ጊዜ ወያኔን ተባብረን ማስወገድ ካልቻልን አገራችን ሙሉ በሙሉ የውሸት፣ የዘረኝነት፣ በአጠቃላይ ርኩሰትና ስነምግባር የጠፋባት አገር ትሆናለች የሚሉት እኝህ አስተያየት ሰጪ፣ ወያኔን ማስወገድ ለነገ የሚያድር የቤት ስራ ባለመኖሩ ትን ትልቁ፣ ሴት ወንዱ፣ ወጣት አዛውንቱ እንዲረባረብ ጠይቀዋል። በተለይ የመከላከያ ሰራዊቱ አገሩ ለዘመናት ስትገነባው የነበረውን የመከባበር፣ እውነት የመናገርና የነጻነት እሴቶች፣ ከሰው ዘር መፈጠራቸውን በሚያጠራጥሩ ሰዎች እየጠፉና እየተመናመኑ በመምጣታቸው፣ እነዚህ ጉዶች ጠራርጎ ማስወገድና በምትኩ በእውነት፣ በስነምግባርና በነጻነት ላይ የተገነባች ኢትዮጵአን ለመመስረት የሚደረገውን ትግል ማገዝ እንዳለበት ባለሙያው ተናግረዋል።


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**
**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**
**በ 7530 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ** እና **በ 9610 KHZ በ 31 ሜትር ባንድ** ላይ የሚደመጥ
መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

**ውድ አንባቢዎቻችን**
**ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን** g7radio@ginbot7.org ***ወይም*** በስልክ ቁጥር 0044- 203-286- 9661